# እ.ኤ.አ. ማርች 1-10/2010 የነበረው

# የአየር ሁኔታ ግምገማ


ባለፉት አሥር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በተለይም በመጀመሪያዎቹ አምስት ቀናት ለወቅቱ ዝናብ መፈጠር መንስኤ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በአብዛኛዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢያችን ላይ የተጠናከረ ገጽታ የነበራቸው ቢሆንም፤ ከአሰሩ ቀን አጋማሽ በኋላ ወደ ሀገሪቱ እየገባ የነበረው እርጥበታማው አየር እየቀነሰ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ አብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቅና ፀሐያማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ሰንብተዋል። ይሁንና ባለፉት አስር ቀናት አብዛኛው ሶማሌ፣ ሐረሪ፣ የደቡብ አሮሚያ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ምስራቃዊው ክፍል፣ ጥቂት የደቡብና የምሥራቅ ትግራይ፤ የደቡብ ምስራቅ አማራ፣ ድሬዳዋና ሀረሪ እንዲሁም አብዛኛው አፋር ከነበራቸው የደመና ሽፋን ከቀላል እሰከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኙ ሲሆን፤ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተስተውሏል፡፡ በ24 ሰዓት ውሰጥ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸው መካከል በቴፒ 90.8፣ በሴሩ 58.8፣ በገለምሶ 49.6፣ በአርሲ ሮቤ 48.0፣ በደገሀቡር 47.2፣ በነገሌ 47.7፣ በሚሌ 42.8፣ በሸዋ ሮቢት 47.7ና 33.6፣ በጎሎልቻ 46.3፣ 35.6 በኮንሶ 37.0ና 32.0፣ በሮቤ 33.0፣ በብላቴ 37.6፣ በጃራ 35.6፣ በዱብቲ 31.2፣ በዶሎመና 35.4 እንዲሁም በቦሬ 30.0 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል።

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከ5-97 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ ከአፋር ዞን 1 እና 3፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሲዳማ፣ የሰገን ህዝቦች፣ የወላይታ፣ የሀዲያና ጉራጌ፣ የደቡብ ኦሞ እንዲሁም የከፋና የቤንች ማጂ ዞኖች ምዕራባዊው ክፍል፤ ከኦሮሚያ ክልል አርሲና ባሌ እንዲሁም የምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ፤ ከሶማሌ ክልል የጅግጅጋ፣ የደገሀቡር፣ የፊቅና የኢፍዲር ዞኖች በተጨማሪም ድሬዳዋና ሀረሪ ከ2-7 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ ከትግራይ ጥቂት የደቡብና የሰሜን ትግራይ፤ ከአማራ ክልል የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል 3 ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ክልል የጂማ እና የምስራቅ ሸዋ ዞኖች፣ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሰሜን ኦሞ ዞኖች እንዲሁም ከአፋር ክልል ዞን 5 ከ5-25 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2 ላልበለጡ ቀናት አግኝተዋል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ፀሐያማና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ ተስተውሎባቸዋል ( ካርታ 1 እና 2 )፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር ከአፋር የዞን 1፣3 እና 5፤ ከኦሮሚያ ክልል አርሲና ባሌ፣ ምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ፤ ድሬዳዋና ሀረሪ፤ ከደቡብ

ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሲዳማ፣ የሰገን ህዝቦች፣ የወላይታ፣ የሀዲያና ጉራጌ እና የደቡብ ኦሞ ዞኖች እንዲሁም ከዋርዴር በስተቀር ሁሉም የሶማሌ ክልል ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ፀሐያማና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ ተስተውሎባቸዋል (ካርታ 3)፡፡


ካርታ1   እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ2 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10 /2018 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 3  እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# እ.ኤ.አ ከማርች 1-10/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ
# በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት ከላይ በተገለፀው መሰረት የተገኘው እርጥበት የበልግ ወቅት የእርሻ እንቅስቃሲ ሲያካሂዱ ለነበሩትና በቡቃያ ደረጃ ለሚገኙ ሰብሎች እንዲሁም የበልግን እርሻ እንቅስቃሴ ዘግይተው ለሚጀምሩ አካባቢዎች ለማሣ ዝግጅትና ለዘር ጊዜ አመቺ ሁኔታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች ለሚገኙ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለመጠጥ ውሀና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት የጎላ ጠቀሜታ እንደነበረው ይታመናል። በሌላ በኩል ከአሰሩ ቀን አጋማሽ ጀምሮ ወደ ሀገሪቱ እየገባ የነበረው እርጥበታማው አየር እየቀነሰ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ አብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በዚህ ጊዜ በመደበኛነት ከሚያገኙት የዝናብ መጠንና ስርጭት እየቀነሰ በመምጣቱ ቀደም ብለው ተዘረተው ለነበሩ የበልግ አዝእርቶችም ሆነ ዘግየተው ለሚዘሩ አካባቢዎች ለማሳ ዝግጅትና ለዘር ጊዜ የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ አሉታዊ ጎን እንደነበረው እሙን ነው (ካርታ 4)።


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ማርች 1 እስከ 10/2018 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# <u>እ.ኤ.አ ከማርች1-10/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ</u>
## <u>በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ</u>

እ.ኤ.አ ከ1-10 ማርች 2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ ስንመለከት ጥቂት የላይኛው ዋቢ ሸበሌ አብዛኛው ገናሌ ዳዋና የታችኛው ባሮ ኮቦ ከፍተኛ እርጥበት ያገኙ ሲሆን፤ የላይኛውና የታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ኦሞ ጊቤና የታችኛው ባሮ አኮቦ፣ የመካከለኛዉና የታችኛው ዋቢ ሸበሌና ገናሌ ዳዋ እንዲሁም የኦጋዴን ተፋሰሶች ከእርጥበታማ እስከ መጠነኛ እርጥበታማ ያገኙ ሲሆን፤ የተቀሩት ተፋሰሶች ከከፊል ደረቅ እስከ ደረቃማ የአየር ሁኔታ ተስተውሎባቸዋል (ካርታ 5)፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2018 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



# <u>እ.ኤ.አ. ከማርች 11-20/2018 የሚኖረው</u>

# <u>የአየር ሁኔታ አዝማሚያ</u>

በመደበኛ ሁኔታ ከማርች አጋማሽ በኋላ የወቅቱ የበልግ ዝናብ አብዛኛዎቹን የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚያደርስበት፤ የመካከለኛውና የደቡብ ኢትዮጵያ ክፍሎች የተጠናከረና የተስፋፋ ዝናብ ማግኘት የሚጀምሩበት ጊዜ ነው፡፡

በማርች በመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት የበልግ ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ከአሰሩ ቀን አጋማሽ በኋላ እየቀነሰ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ አብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቅና ፀሐያማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ሰንብተዋል። ይህም ሁኔታ በሚቀጥሉት የመጀመሪዎቹ አስር ቀናት እየቀጠለ የሚሄድ ቢሆንም፤ ከአስሩ ቀን አጋማሽ ጀምሮ ከዕለት ወደ ዕለት የእርጥበት መጨመር እንደሚኖር የተተነበዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚህ ጋር ተያይዞ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ወቅታዊው ዝናብ በመጠንም ሆነ በሥርጭት ከአስሩ ቀን አጋማሽ በኋላ የወቅቱ ዝናብ ተጠቀሚ አካባቢዎች ላይ እንደሚጨምር ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም በደቡብ፣ በደቡብ በምሥራቅ፣ በምስራቅና በጥቂት የደቡብ ምዕራብና የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ዝናብ የመኖር ዕድል ይኖራል።

በአጠቃላይ <u>አብዛኛው ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሲዳማ፣ የሰገን ህዝቦች፣ የወላይታ፣ የሀዲና ጉራጌ፣ የደቡብ ኦሞ እንዲሁም አልፎ አልፎ የከፋና የቤንች ማጂ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል የጂማ፣ የምዕራብና የሰሜን ሸዋ፣ አርሲና ባሌ፣ የጉጂና የቦረና ዞኖች፣ ምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ፤ አዲስ አበባ፤ ከዋርዴር በስተቀር ሁሉም የሶማሌ ክልል ዞኖች፤ ድሬዳዋና ሀረሪ፤ የምሥራቅና የደቡብ ትግራይ፤ ከአማራ ክልል የደቡብና የሰሜን ወሎ እንዲሁም የሰሜን ሸዋ፤ በተጨማሪም ከአፋር ዞን 3 እና 5 በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ የሚያገኙ ቢሆንም፤ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ከመደበኛው በላይ ዝናብ የማግኘት ዕድል የኖራቸዋል። በሌላ በኩል የተቀሩት ሀገሪቱ ክፍሎች ደረቃማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው የቆያሉ።</u>

## እ.ኤ.አ. ከማርች 11-20/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

## በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ ከማርች ሁለተኛው አስር ቀናት አጋማሽ በኋላ በአብዛኛው የበልግ ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ በተለይም የደቡብና የመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች በመጠንም ሆነ በቦታ የተሻለ እርጥበት የሚያገኙበት ወቅት ሲሆን፣ ይህም ሁኔታ ለበልግ ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሀ አቅርቦት በጎ አስተዋጽኦ የሚያበረክትበት ጊዜ ነው፡፡ በተጨማሪም በደቡብና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ አርብቶ አደርና የከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት የግጦሽና የመጠጥ ውሀ አቅርቦትን ከማግኘት አንጻር የተሻለ ዕድል የሚያገኙበት ጊዜ ሲሆን፤ በሌላ መልኩ ከበልግ ወቅት ዝናብ ባህሪ አኳያ ደረቅ ሰሞናት የሚስተዋልበት ጊዜም ነው፡፡

በመሆኑም በተሰጠው የማርች ሁለተኛው አስር ቀናት የአየር ሁኔታ ትንበያ መሠረት በተለይም በመጀመሪያዎቹ የአስር ቀናት ደረቅ ሰሞናት እንደሚያመዝን ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ በተለይም ከባለፈው አስር ቀናት አጋማሽ በኋላ ከተስተዋለው ተከታታይ ደረቅ ሰሞናት ጋር ተዳምሮ የውሃ እጥረቱን ሊያባብስ እንደሚችልና ይህም ሁኔታ በሰብሎች ሁለንተናዊ እድገትም ሆነ በእንስሳት ልማት ላይ የራሱ አሉታዊ ጎን ሊያሳድር እንደሚችል ግምት መውሰድ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም የሚጠበቀው ደረቃማ የአየር ሁኔታ አስቀድመው ለተዘሩና በተለያ ዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውሀ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንፃር አሉታዊ ጎን ሊኖራቸው ^ንደሚችልና ከቀኑ ከፍተኛ ሙቀት ጋር ተያይዞ የሚገኘው የአፈር ውስጥ እርጥበት በትነት ሊቀንስና ብሎም ሊደርቅ የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮች ይህንኑ የአፈር ውስጥ የውሃ እጥረት እንዳይከሰትና በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰብሎች ጉዳት እንዳይደርስባቸው አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ደረቃማው ሁኔታ የመኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያስከትል እንደሚችል ግንዛቤ በመውሰድ ባለፉት የበልግ ቀናት የተገኘውን የዝናብ ውሃ በአግባብ በመጠቀምም ሆነ ሌሎች አማራጮችን ለመመልከት የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከማርች 11-20/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስርት ቀናት በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊኖር የሚችለውን ተፅኖ ስንመለከት የላይኛው አፋር ደናክል፣ የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽ፣ አባይ፣ ስምጥ ሸለቆና ዋቢሸበሌ፣ አብዛኛው የኦሞ ጊቤ፣ የባሮ አኮቦና የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች መጠነኛ እርጥበት እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ ለውሃው እንቅስቃሴ በጣም ጠቃሚ ስለሆነ በተቻለ መጠን በጥብቅ ክትትልና በጥንቃቄ መጠቀም እንደሚገባ እናሳስባለን፡፡